# ዋልታ-የቅጥፈት እምቢልታ!

ከፍርዱ ዘገዬ

ኧረ - እየተስተዋለ!?
ሚዛናችሁ በጣም ቀለለ፤
ሰማዕቱ የኔሰው እብድ ነው ተባለ?!
ወያኔ አይሰጠው ቀጥል የለ።

የወያኔ ቱልቱላ ዋልታ፣
የግፈኞች ጋሻ መከታ፣
የቀጣፎቹ ምሽግ ዋሻ፣
የፈጠራ ውሸት ማናፈሻ፣
በጣም ለየለት ልብሱን ጣለ፣
ጤነኛውን ዕብድ ነው አለ።

የዋልታ ካድሬዎች!
የሀሰት ጠበቆች፤
ማን አለብን ብለው እየገነፈሉ፣
እንዲያው በለብለብ ሳይሞቁ እየፈሉ፣
በጠሉት ሁሉ ላይ ስም ይለጥፋሉ፣
የማይሉት የለም በሉ ከተባሉ፣
የሀሰት ምሥክር ደፍረው ይቆጥራሉ።

ብርቅና ድንቆችን፣
የሕዝብ ልጆችን፣
የግፉዐን ድምፆችን፣
እነእሥክንድር ነጋን፣
ሙሉዓለም አንዳርጌን፣
ሳይፈሩ፣ ሳያፍሩ ወንጅለዋቸዋል፣
አሸባሪ የሚል ቅጥል ቀጥለዋል፣
የኔሰው ገብሬንም እብድ ነው ብለዋል፤
እብድ ማን እንደሆን ለይቶላቸዋል፤
የወያኔ ቀውሶች በግልጥ ቀውሰዋል፣
ሰብአዊ ኅሊና ፍፁም ሸሽቷቸዋል።

ወገኖች ምከሩ፣ ቁናው ዙሩን አልፏል፣
ከዚህስ የባሰ ምን ጥቃት ይመጣል?

የኔሰው ሰማዕቱ ለፍትህ የተሰዋ፣
ደሙ ያስተጋባል ሆኖ እንደመረዋ።
አዎ! መረዋ ነው፣ የየኔሰው ደሙ፣
ነቃ ነቃ በሉ የተኛችሁ ሁሉ።

ይጮሀል፤ ይጣራል፤ ምውት እንዲነቃ፣
በወኔ እንዲነሳ ዞትር ከሚጠቃ።

በሽብር አዋጁ ሽብር በሸፈነው፣
ማሰብ፣ ማሰላሰል፣ ማለምም ክልክል ነው፣
መሰብሰብ፣ መሰለፍ፣ መቃዎም ዘበት ነው፤
አዋጅ ያልወጣበት አንድ ነገር ቢኖር፣ እራስን ማትፋት ነው።

ይህ ዓይነቱ ሥርዓት ከሥርዓት ተቆጥሮ፣
እንገፋዋለን ኑሮን እንደ ኑሮ፣
ይህ ሥርዓት አይደለም፤ የሥርዓት አሻሮ፣
በውሸት ላይ ውሸት፣ ቅሌት ተደምሮ።

የወያኔ ዋልታ እብድ እያለ ሲያፏጭ፣
ጀግናውን፣ ሰመዕቱን የሌለውን ልዋጭ፣
መቃጠል፣ ማቃጠል የለውም አማራጭ።
በየኔሰው ጉዞ ሩቅ ለሚሄዱ፣
መቃጠል፣ ማቃጠል ፅድቅ ነው መንገዱ።

በወያኔ ቋንቋ በአዲሱ አማርኛ፣
የሚቃወመውን ይለዋል ነውጠኛ፣
ትንሽ ካንጓጠጠም ይባላል ነፍጠኛ፣
በልቶ ካላበላም ይሉታል ሙሰኛ፣
ይህ ነው ዴሞክራሲው የሰው መመዘኛ?
ማሽቀንጠር አለብን ይህንን መርዘኛ።

ያች ቀን ስትደርስ ተገፍታ፣ ተገፍታ፣
ከምንም አያድን የወያኔ ዋልታ፣
ወገኔ ተጠንቀቅ አትሁን እምቢልታ፣
የሚሆነው ላይቀር በሆድ አትረታ።

የየኔሰው ሰዎች እግዚአብሔር ያጥናችሁ፣
የሁላችንም ነው መሪር ሐዘናችሁ፣
የየኔሰው መልዕክት ምንጊዜም ክቡር ነው፣
ከጴጥሮስ ሰማዕቱ፣ ረድኤት-በረከት እዚአብሔር አይለየው።

በየኔሰው ወኔ የምትታጠቁ፣
ሞትማ ካልቀረ ጥላችሁ ውደቁ።